# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ወጣት ክንፍ ድርጅት (ኢሕአፓ ወክንድ)

## Ethiopian Peoples Revolutionary Party Youth League (EPRP YL)

## የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታ ፓርቲ ወጣት ክንፍ መግለጫ

ግንቦት 2007 ዓ.ም

### <u>የወያኔ አገዛዝ በኢትዮጵዊያን ወጣቶች ላይ የሚያደርሰውን አፈና አጥብቅን እናወግዛለን !</u>

ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጉያ የፈለቀው ወጣት ትውልድ ትናንት በህብረተሰቡ ውስጥ ሥር ሰደው የነበሩትን ቅራኔዎች በድፍረት መዞ እንዳውጣቸው ሁሉ ዛሬም ጎጠኛው የወያኔ አገዛዝ በህዝብ ላይ እያደረሰ ያለውን ግፍና በደል አጥብቆ የመታገል ታሪካዊ  አደራ ተጥሎበታል። በአምባገነኖች አፉ ተለጉሞ፣ ሙብቱ ተገፎና ተረግጦ የሚኖር ሕዝብ ስብእናውን ለማስከበር በአለው አቅምና ባመቸው መንገድ ሁሉ መታገል የግድ ይለዋል።

የህብረተሰቡ መሠረታዊ ጥያቄዎች በውል ተጢነው በሰላምና በዲሞክራሲያዊ መንገድ እስካልተፈቱ ድረስ ይዋል ይደር እንጂ ማህበራዊ ቅራኔዎች ፈጥጠው መውጣቸው አይቀርም። ግፈኛው አገዛዝ ልክ እንዳለፉት አምባገነኖች ወታደራዊ ጡንቻ አለኝ ብሎ ሲኩራራ ህዝበ በአንድነት ቆርጦ ከተነሳ የታጠቀው ብረት እንደሰም መቅለጡና በትዕቢት የተወጠረ ልቡም እንደጎማ ተንፍሶ አግሬ አውጭኝ ማለቱ አይቀሬ ነው።

የኢትዮጵያ ወጣት ትውልድ  ለሀገርና ለወገን ጥቅም እስከሆነና እስካመነበት ድረስ ችግርና መከራን ይችላል። በአንጻሩ ደግሞ የሕዝብና የሀገር ህልውና ሲነካ፣ ክብሩ ሲደፈር፣ አንድነቱ ሲናጋ፣ ስብእናው ሲደፈር፣ አሻፈረኝ! በቃኝ ብሎ ማምረሩና ማመፁ የሚጠበቅና አኩሪ ኢትዮጵያዊ ልማዱ ነው።

ኢትዮጵያዊ ክብሩነና ነፃነቱን ለማንም አሳልፎ መስጠት አይፈልግም። ነፃነትትና ክብር ዋጋቸው ቀላል እንዳልሆነም አጥብቆ ይገነዘባል። ትግልም መስዋእትነትን እንደሚይጠይቅ ጠንቅቆ ያውቃል።

በጎጠኝነት የታወሩ የወያኔ መሪዎች ፍላጎት ሀ እና ፐ ወይም "አልፋና ኦሜጋ" ብቸኛ የመንግሥት ሥልጣን ባለቤት ሆነው ለመኖር ነው። ነገር ግን በጠብ-መንጃ የያዙት ሥልጣን በኢትዮጵያዊያን ፈቃድ ተጠብቆ ሊቆይ እንደማይችል ያውቃሉ። የሚያወጧቸው ህጎችም እነሱ ሌሎችን ለመከፋፍል፣ ለማሰርና ለመግደል የሚገለገሉባቸው እንጂ ህጋዊነትን ለማስከብር የሚያግዙ ህዝብን በሰላም ለማስተዳደር የሚያገለግሉ አይደሉም።

ለዚህም ጥሩ ምሳሌ የሚሆነው በቅርቡ ገዥው ቡድን አሸናፊነቱን አስቀድሞ ባረጋገጠበት፣ ምርጫ ብሎ በሚጠራው ወያኔያዊ ቧልት፣ የራሱን ጥላ እንኩዋን የማያምነው የወያኔ ቡድን የደህንነት አማካሪ ተብየው የትግራይ ወጣቶችን ሰብስቦ ያሰማው መርዘኛ ንግግር  "እኛ ካልተመረጥን የትግራይ ሕዝብ  ማለቁ ነው፤ የጀምርነው ልማት በተቃዋሚዎች ሊድናቀፍ ነው " የሚል ነበር።

ዓላማው የትግራይን ወጣት በዘረኛ መርዙ ለመክተብና ቀድሞም ለሻዕቢያ ጦርነት ተማግደው ለስልጣን እንዳበቁት ሁሉ፣ አሁንም የወንጀላቸው ተባባሪ ለማድረግና ከቀረው ኢትዮጵያዊ ወገኑ አንድ ሆኖ እንዳይቆምና ዘላቂ ቁርሾ ለመፍጠር ነው። እንዲህ አይነቱ መርዘኛና ወሮበላ ቡድን ነው ታሪካዊቷን ኢትዮጵያ እየገዛ ያለው። ይህም ስለሆነ ነው ወያኔ የተባለውን ታሪካዊ መርገም ከነግሳንግሱ ነቅሎ መጣል በወራሪ ሃይል ላይ ሊኖር ከሚገባው ቁርጠኝነት ተለይቶ ሊታይ የማይገባው። ከቆዳ ቀለም ባሻገር የሁለቱም ዓላማ ኢትዮጵያን መበታተንና በመጨረሻም ማጥፋት ነውና።

ይህ የወያኔ ህልውና ስጋ-ወደሙ የሆነ መርዝ እየተሰራጨ ያለው በትግራይ ወጣቶች ብቻ ሳይሆን በሀገሪቱ ያሉ ከከፍተኛ አስከ ዝቅተኛ የትምህርት ተቋማትም ጭምር ነው። በአንድ ወቅት ብዙ ታላቅ ራዕይ የነበራቸው ምሁራን ይፈልቁበት የነበረው ኢ.አ. ዩኒቨርስቲ እንኳ ከዚህ አሳዛኝና አሳፋሪ ወያኔያዊ ወረርሽኝ ሰለባ ከመሆን አላመለጠም።

የዜግነት ሙብቱን ገፍፎ፣ ወጣቱ በሀገሩ ሰርቶ መኖር እንዳይችል ሀገሪቱን ወደ ማህበራዊ ሲኦል ለውጦ አነሆ ቃላት ሊገልፁት የማይችሉት ሞት፣ሰቆቃና ውርደት ራስን በራስ ከማጥፋት የማይተናነስ ስደት ዳርጓቸዋል። እናት ልጇ እንደፋሲካ በግ በጠራራ ፀሃይ ሲታረድ፣ ጎማ በአንገቱ-ቷ ዙሪያ ገብቶ ሲቃጠል በቴሌቪዥን መስኮት የምታይበት ሁኔታን ፈጥሯል።

Tel: 202-291-5832 5309 Georgia Ave. NW 2nd Fl. Washington DC 20011

E-mail: eprpylnew @gmail.com Website: www.eprpyl.com

*ወያኔ የእያንዳንዱን ኢትዮጵያዊ የዜግነት መብት በየእለቱ እየጨፈለቀ የገነባው የዚህ ህግ- አልባ ሥራዓት መሠረቱ ነፍጥ ብቻ አይደለም። ቆስቁሰው የሚያራግቡት ዘረኝነት ዋነኛው ስንቃቸው ጭምር ነው። የሕዝቡ ድርና ማግ የሆነውን ኢትዮጵያዊነትን በዘር እርከን እየሸነሸኑ በተዋረድ የፈጠራችው ድንበሮች የሁሉም ብሔረሰቦች እኩልነት የሚረጋገጥባቸው አስተዳደራዊ ከልሎች ሳይሆኑ አንዱ በሌላው ላይ በጥላቻ እንዲነሳ ለማደርግ ሆን ተብለው የተወጠኑ የጥቅም ልዩነት የሚደረግባችው የዘረኝነት ወጥመዶች ናቸው። የኢትዮጵያ ወጣቶች ባጠቃላይ በተለየም ደግሞ ትግሪኛ ተናጋሪ ወጣቶች በዚህ ወያኔያዊ መሠናክል ውስጥ ገብተው በአያሌ ዘመናት የገነቡትን ኢትዮጵያዊነት ለአንዴም ...... ለሁሌም ላለማጣት ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ይገባቸዋል ሲል የኢሕአፓ ወጣት ክንፍ ድርጅት(ኢወክንድ) አጥብቆ ያሳስባል።*

*ወያኔ በሃይል፣ በፕሮፓጋንዳና በጥቅም ሕዝብን እየለያየ ለመግዛት የከፋፈለው አገር አንድነቱ በቀላሉ ሊመለስ አይችልም። በጎጠኛው የወያኔ ቡድን አገዛዝ ሥር ለወደቀችው ኢትዮጵያም መስዋአእትነት ለመክፍል ዝግጁ የሆኑ ኢትዮጵያዊ ወጣቶች በሙሉ የወገኖቻችንን ሰቆቃ ለመታደግ ዛሬውኑ አንሰባሰብ ሲል የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ ፓሪቲ ወጣት ክንፍ ድርጅት(ኢወክንድ) የትግል ጥሪውን ያቀርባል።*

*ለኢትዮጵያ አንድነት ተቆርቃሪ የሆኑ አገር ወዳድ ኢትዮጵያዊያንም የነፃነት ትግሉ እንዲጎለብት ለማድረግ ያለባቸውን ህላፊነት ሳይዘነጉ በሚችሉት መንገድ ሁሉ ኢወክንድን በመደገፍ የዜግነት ግዴታቸውን እንዲወጡ ያሳስባል።*

*ሁሉም የፖለቲካ አስረኞች ያለምንም ቅድመ ሁኔታ አሁኑኑ ይፈቱ!*

*የወያኔ አገዛዝ በተባበረ የሕዝብ አመፅ ይወገዳል!*

Tel: 202-291-5832 5309 Georgia Ave. NW 2nd Fl. Washington DC 20011

E-mail: eprpylnew @gmail.com Website: www.eprpyl.com